10

፯ኛ ዓመት ቁጥር 13
7th Year No. 13

ባህር ዳር መጋቢት 23/1994 ዓ/ም
Bahir Dar 13th April 1.2002

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspice of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 2.96
Unit price ----------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓ/ም
የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 69/2002
Revised Proclamation for Establishing the Judicial Administration Commission Amhara National Regional State

አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት ነፃ የዳኝነት አካል የተቋቋመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ቢሆን መንግስቱ የተረጋገጠውን የዳኝነት ነፃነት መር በተሟላ መንገድ እውን ለማድረግ ከሚያስችሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የዳኞች አስተዳደርን ከማናቸውም አካል ተፅዕኖ ገለልተኛ ሆኖ እንዲደራጅ ማድረግና ሥራውንም በአግባቡ ማከናወኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በዚህም ምክንያት የየደረጃውን ዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ ስንብትና ዲሲፕሊን አስመልክቶ በተለይ መደንገግ በማስፈለጉ፣

Proclamation No. 69/2002

Revised proclamation for Establishing the Judicial Administrations Commission Amhara National Regional State

WHEREAS, an independent judiciary is established under the Constitution of the Amhara National Regional State;

WHEREAS, one, and the major, of the fundamental factors that help to realize the Constitutionally guaranteed independence of the judiciary is to have a neutral judicial administration which is organized in a manner free from the influence of Government organs or officialdom so that it would properly discharge its duties;

WHEREAS, it has therefore become necessary to enact special legal provisions concerning the recruitment of judges at all levels, as well as promotion, appointment, transfer, discharge and discipline of judges;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓም ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ሕገ መንግሥት" ማለት በ1994 ዓ/ም ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት ነው።
2. "ምክር ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ነው።
3. "ክልል ጉባዔ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልል ደረጃ የተቋቋመው የዳኞች አስተዳደር አብይ ጉባዔ ነው።
4. "የዞን ጉባዔ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔረሰብ ወይም በዞን አስተዳደር ደረጃ የሚቋቋም የዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ ነው።
5. "ፍርድ ቤት" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 67 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የተዋቀሩትን የክልል፣ የከፍተኛና የወረዳ ፍ/ቤቶችን ያጠቃልላል።
6. "ዳኛ" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 68 ድንጋጌ መሠረት በየደረጃው በተዋቀሩ የክልሉ ፍ/ቤቶች ውስጥ የዳኝነት ተግባራትን እንዲያከናውን በም/ቤቱ የሚሾም የተፈጥሮ ሰው ነው።

NOW THEREFORE, The Amhara National Regional State Council in accordance with Article 49(3)(1) of the Revised National Regional Constitution of November 5, 2001, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
General

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as the "Revised proclamation for Establishing the Judicial Administration Commission of Amhara National Regional State proclamation No. 69/2002."

2. **Definitions**

In this proclamation unless the context otherwise requires:-

1. "Constitution" means the Revised Constitution of Amhara National Regional State of 2001.
2. "Council" means the Amhara National Regional State Council.
3. "Regional Commission" means the Judicial Administration Commission established at Regional level by this Proclamation.
4. "Zonal commission" means the sub-judicial Administration Commission to be established by this proclamation at Nationality or Zonal Administration level.
5. "Court" means the courts established at various hierarchies including Regional, High and Woreda Courts pursuant to Article 67(1) of the Constitution.
6. "Judge" means a natural person appointed by the Council, to carry out judicial duties in all Courts established at various hierarchies in accordance with article 68 of the constitution.

6. "ሬጅስትራር " ማለት በክልሉ ፍ/ቤቶች ውስጥ አስተዳደራዊና ችሎት ነክ ተግባራትን እንዲያከናውን በክልሉ ጉባዔ የሚሾም የተፈጥሮ ሰው ነው::

7. "ተከላካይ ጠበቃ" ማለት በክልሉ ፍ/ቤቶች በከባድ ወንጀል የተከሰሱና ጠበቃ አቁመው መከራከር የማይችሉ ሰዎችን በጠበቃነት ወክሎ እንዲከራከር በክልሉ ጉባዔ የሚሾም ባለሙያ ነው::

ክፍል ሁለት

ስለዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም ፣ ተዋፅኦ፣ ኃላፊነትና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

3. ስለ ክልል ጉባዔ መቋቋም

የክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት "የክልል ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

4. ስለ ጉባዔው አባላት ተዋፅኦና ጥንቅር

የክልል ጉባዔ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ይሆናሉ::

1. የጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ..... ሰብሳቢ
2. የጠ/ፍ/ቤት ም/ፕሬዚዳንት ..... አባል
3. የም/ቤቱ ሁለት ተወካዮች ..... አባላት
4. አንድ የጠ/ፍ/ቤት ዳኛ ..... አባል
5. ሁለት የከፍ/ፍ/ቤቶች ዳኞች ..... አባላት
6. ሁለት የወረዳ ፍ/ቤቶች ዳኞች..... አባላት
7. የክልሉ ፍትህ ቢሮ አንድ ተወካይ... አባል

7. "Registrar" means a natural person appointed by the Regional Commission to carry out administrative and court related duties in the courts of the Region.

8. "Defense Lawyer" means a legal professional appointed by the commission to act as lawyer for those charged with heave criminal offences by courts of the Region and who can not afford to hire their own lawyers.

PART TWO

The Judicial Administration Commission's Establishment, Composition, Responsibility and Meeting Procedures

3. Establishment of Regional Commission

The Regional Judicial Administration Commission hereinafter referred to as "the Regional Commission" is hereby established in accordance with the provisions of Article 2(3) above.

4. Composition of Members of the Commission

Pursuant to this proclamation, members of the Regional Commission shall consist of :

1. President of the Supreme Court ..... Chairperson
2. V/President of the Supreme Court ..... Member
3. Two representatives of the Council ..... Members
4. A Supreme Court Judge ..... Member
5. Two High Court Judge ..... Members
6. Two Woreda Court Judges ..... Members
7. A Representative of the Regional Justice Bureau ..... Member

8. የክልሉ ጠበቆች ማህበር አንድ ተወካይ ..... አባል

9. የክልሉ ሴቶች ማህበር አንድ ተወካይ ..... አባል

5. ስለ ክልሉ ጉባዔ አባላት አመራረጥ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተመለከቱትና በክልል ጉባኤ አባላት የሚሳተፉት ሁለት የምክር ቤቱ ተወካዮች የክልሉ ሕግ አውጭ ምክር ቤት አመራርና የህግ አስፈፃሚው አካል አባላት አለመሆናቸው ተረጋግጦ በምክር ቤቱ ተመርጠው ይሰየማሉ::

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4,5 እና 6 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱትና በክልል ጉባዔ አባልነት የሚሳተፉት ዳኞች በምርጫ የሚሰየሙ ሲሆን አመራረጡን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል::

6. የክልል ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ተጠሪ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ. በየእርከኑ ለተቋቋሙ ፍ/ቤቶች በዳኝነት የሚሾሙ ዕጩ ዳኞችን የሙያ ብቃትና የሥነ ምግባር ሁኔታ እየገመገመ ይሾሙ ዘንድ ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል ሲሾሙም ይመድባል፣

ለ. ዳኞችን የሥራ ቦታ ዝውውር፣ አበል፣ የደረጃ እድገት፣ ህክምናና የመሣሰሉትን አስመልክቶ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ይወስናል፣

ሐ. ዳኞችን በተመለከተ የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል፣

መ. በጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞችና በየዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች ላይ የሚቀርቡትን የዲስፕሊን ክሶች መርምሮ ይወስናል፣

8. A representative of the Bar Association of the Region ..... Member

9. A Representative of the Regional women's Association ..... Member

5. Selection of the Regional Commission Members

1. Two representatives of the Council indicated in Article 4(3) of this proclamation shall be selected by the Council to partake in the Regional Commission following confirmation that they are not members of the Regional council's Legislative and Executive bodies.

2. Judges indicated in Article 4 (4,5 and 6) of this Proclamation who are to serve as members of the Regional Commission shall be elected by vote; the selection of these judges shall be carried out according to the directive to be issued by the President of the Supreme Court of the Region.

6. Powers and Duties of the Commission

1. Being accountable to the Council, the Regional Commission in accordance with this Proclamation, shall have the following powers and duties:

A. To assess the conduct and professional competence of candidate judges with the quality for judgeship in the various hierarchical courts and present them for appointment, to the Council, and to place them when they are appointed.

B. To decide on matters concerning the transfer, allowance, promotion, medication and other issues of judges.

C. To prepare and present to the Council the regulation on the conduct and discipline of judges, and to execute same when approved.

D. To examine and decide on disciplinary charges against judges of the Supreme Court and the presidents of the Zonal High Courts;

ሠ. ከዞን ንዑሣን ጉባዔዎች በየጊዜው የሚተላለፉትን የዳኞች ዝውውር፣ ዲስፕሊንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚመለከቱ የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔዎች መርምሮ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል፣

ረ. ሬጅስትራሮችንና ተከላካይ ጠበቆችን መርጦ ይሾማል፣ ይመድባል፣ የደመወዝና አነርሱን የሚመለከቱ ሌሎች ተዛማጅ የአስተዳደር ጉዳዮችን ተመልክቶ ይወስናል፣ እንደአስፈላጊነቱ የአፈፃፀም መመሪያዎችንም ያወጣል፣

ሰ. ከሥራ ባህሪው ጋር የተያያዙ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

2. የክልሉ ጉባዔ በብሔረሰብ አስተዳደሮች የሚያገለግሉ አፈጩ ዳኞችን ለሹመት ለም/ቤቱ ከማቅረቡ በፊት ከሚመለከታቸው የብሄረሰብ ምክር ቤቶች አስተያየት መጠየቅ አለበት፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጉባዔ የጠቅላይና የከፍተኛ ፍ/ቤቶች አፈጩ ዳኞችን ሹመት ለም/ቤቱ ከማቅረቡ በፊት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የፌዴራሉን ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አስተያየት መጠየቅ አለበት፣

4. አንድ ዳኛ ከሥራ ሊያሰነሳ የሚችል ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ወይም የሥነ ምግባር ጉድለት ፈጽሟል ተብሎ ክስ ሲቀርብበት ጉዳዩን የክልሉ ጉባኤ መርምሮ አስኪወስን ድረስ ዳኛው በሥራው ላይ ቢቆይ በደል ያደርሳል ብሎ ካመነ ጉባዔው ለጊዜው ከሥራ እግዱ ሊያቆየው ይችላል።

5. ጉባዔው ክሱን ከመረመረ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ለጊዜው ታግዶ የቆየውን ዳኛ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት ከሥራ ኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ እንዲቶ ውሣኔው እንዲፀድቅ ለም/ቤቱ ያቀርባል።

E. To examine, approve, amend and repeal the first stage decisions regularly passed by Zonal sub-commissions concerning the discipline and transfer of judges and other matters .

F. To select, appoint and place registrars and defense lawyers; to examine and determine salary issues and related administrative matters; to issue directives as deemed necessary.

G. To discharge other legal activities that bear relevance to the work.

2. Prior to presenting the Council with candidate judges for appointment to serve in the Nationality Administrations, the Regional Commission shall have to request the opinion of the concerned Nationality Councils.

3. Without Prejudice to sub-article 2 of this Article, the Regional Commission, prior to presenting the Council with candidate judges to be appointed as judges of the Supreme and High Courts, shall request the opinion of the Federal Judicial Administration Commission as provided for in Article 68(3) of the Constitution.

4. Where a judge commits a serious disciplinary offence or charged with a breach of conduct, which causes the Commission to believe that the continued presence of the judge brings harm, the Commission shall suspend the judge until the regional Commission examines and decides upon the case.

5. Where the commission, following a consideration of the case, finds the suspended judge guilty of the offence, it shall decide to relive the judge permanently and present its decision to the Council for approval.

7. ስለ ጉባዔው የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

1. የክልሉ ጉባዔ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

2. ከጉባዔው አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣

3. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምፁ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

4. የዲስፒሊን ክስ የቀረበበት ማናቸውም የጉባዔ አባል የሆነ ዳኛ እርሱን የሚመለከት ክስ ሲመረመር በስብሰባው ላይ አይገኝም፣

5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

8. ስለ ዞን ጉባዔ መቋቋም

የዞን ዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር በተተረጐመው መሠረት "የዞን ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

9. ስለ ዞን ጉባዔ አባላት ተዋጽኦ ጥንቅር

1. የዞን ጉባዔ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ. የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ..... ሰብሳቢ

ለ. ሁለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች ..... አባላት

ሐ. ሶስት የወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች ..... አባላት

7. Meeting procedures of the Commission

1. The Regional Commission shall hold a regular meeting once every two months; however, it may meet at any time where found necessary.

2. There shall be a quorum where two-third of Commission members are present.

3. Decisions of the Commission shall be passed by a majority vote; in case of a tie, however, the chair-person shall have a casting vote.

4. A judge who is a member of the Commission, and against whom disciplined proceedings are instituted, may not sit in meetings of the Commission while his case is under investigation.

5. Without prejudice to the provisions of sub-articles 1-4 of this Article, the Commission may draw up its own rules of meeting procedure, as deemed necessary.

8. Establishment of Zonal Commission

Pursuant to Article 2(4) of this Article, the Zonal Judicial Administration Sub-Commission hereinafter referred to as "Zonal Commission", is hereby established by this Proclamation.

9. Composition of Zonal Commission Members

1. Pursuant to this Proclamation, the Zonal Commission shall have the following members:

A. Zonal high court President ..... Chairperson

B. Two high court judges ..... Members

C. Three woreda court judges ..... Members

መ. ከሚመለከተው ዞን ፍትህ
ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ..... አባል

ሠ. ከክልሉ ጠበቆች ማህበር
የዞን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አንድ
ተወካይ ..... አባል

ረ. በብሔረሰብ አስተዳደሮች ሁለት
የብሔረሰብ ም/ቤት አባላት፣
ምክር ቤት በማይቋቋምባቸው
የዞን አስተዳደሮች ደግሞ የክልል
ጉባኤ አባላት ያልሆኑ ሁለት
የክልል ም/ቤት ተወካዮች ..... አባል

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ እስከ ፊደል ተራ ቁጥር ሐ በተደነገገው መሠረት በዞን ጉባዔ አባልነት እንዲያገለግሉ የተሰየሙ የከፍተኛና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 ድንጋጌዎች መሠረት በክልል ጉባዔ አባልነት በተጨማሪ ሊመረጡ አይችሉም::

10. ስለዞን ጉባዔ አባላት አመራረጥ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የተመለከቱትና በዞን ጉባዔ አባልነት የሚሳተፉት የከፍተኛ ፍ/ቤትና የወረዳ ፍ/ቤቶች ዳኞች በምርጫ የሚሰየሙ ሲሆን አመራረጡን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል::

11 የዞን ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

የዞን ጉባዔ በዚህ አዋጅ መሠረት ተጠሪነቱ ለክልሉ ጉባዔ ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ጥፋት በፈፀሙ የዞን ከፍተኛና የወረዳ ፍ/ቤቶች ዳኞች ሬጅስትራሮችና ተከላካይ ጠበቆች ላይ አስፈላጊውን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል:: ሆኖም የተፈፀመው ጥፋት ከሥራ የሚያስነሳው ሆኖ ሲገኝ ለጊዜው ከሥራ እግዶ ደመወዙን እየከፈለ ጉዳዩን ከተገቢው የውሣኔ ሃሳብ ጋር ለክልሉ ጉባዔ ያስተላልፋል፤

D. A representative of concerned Zonal Justice branch office ..... Member

E. A representative of a Zonal Bar Association Branch office of the Region..... Member

F. Two members of the nationality council in the nationality administrations or two regional council representatives who are not regional commission members in those zonal administrations where councils are not established ..... members

2. Pursuant to the provisions of sub-article 1(A-C) of this Article, high Court and Woreda court Judges nominated to serve as members of the Zonal Commission shall not also serve as members of the Regional Commission in accordance with the provisions of Article 4(5 and 6) of this Proclamation.

10. Selection of Zonal Commission Members

Pursuant to Article 9 (1 and 2) of this proclamation, the High Court and Woreda Court Judges to serve as members of Zonal Commission shall be nominated by election; the election process shall be executed by the directive to be issued by the president of the Supreme Court of the Region.

11. Power and Duties of Zonal Commission

Being accountable to the Regional Commission, the Zonal Commission shall have the following powers and duties:

1. To take the necessary disciplinary measures against Zonal High and Woreda Court judges, registrars and defense lawyers where these are found guilty of offence; however, where the committed offence is not of the kind that warrants firing, it may suspend the offenders while paying them salaries, and transmit the case together with appropriate suggestions to the Regional Commission for a final decision.

2. የዳኞችን ዝውውር በሚመለከት ለክልሉ ጉባዔ የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

3. የይግባኝ ቅሬታ የሚቀርብባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔዎች በወቅቱ ገልብጦ ከቅሬታ ማስሚያ አቤቱታዎቹ ጋር ለክልሉ ጉባዔ ያስተላልፋል፤

4. በተቋቋመበት ዞን ውስጥ የወረዳ ፍ/ቤት ሰብሳቢ ዳኞችን መርጦ ይመድባል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፤

5. በብሔረሰብ አስተዳደር የሚገኝ የዞን ጉባኤ በብሔረሰብ አስተዳደር ውስጥ ስለሚሾሙት ዳኞች ለብሔረሰቡ ምክር ቤት ዘገባ ያቀርባል፤

6. ከሥራ ባህሪው ጋር በተያዘ በክልሉ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. To make suggestions to the regional Commission about cases concerning transfer of judges.

3. .To promptly transmit to the Regional Commission the first stage decisions against which appeals have been lodged, along with the copy of the first stage decisions and the appeals of discontent.

4. To select and place presiding judges of Woreda Courts of the concerned Zone, and to monitor their activities.

5. The Zonal Commission in a Nationality Administration shall report to the Nationality Council about the judges to be appointed to serve in the Nationality Administration.

6. To carry out other activities as are given by the Regional Commission, which are relevant to the work.

12. ስለዞን ጉባዔ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

የዞን ጉባዔ መደበኛ ስብሰባውን በየወሩ አንድ ጊዜ የሚያከናውን ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል። ዝርዝሩን በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ሥር የክልሉን ጉባዔ የስብሰባ ሥነ- ሥርዓት አስመልክቶ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንዳስፈላጊነቱ በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።

12. Meeting procedure of Zonal Commission

The Zonal Commission shall hold its regular meeting once every month; however it may meet for emergency sessions any time where found necessary. Concerning the particulars, provisions of meeting procedures of the Regional commission under Article 7 of these proclamations shall similarly be applicable as it may be necessary.

ክፍል ሶስት

የጉባዔ ሰብሳቢዎች ሥልጣንና ተግባር

PART THREE

Powers and Duties of Commission Chairpersons

13. የክልል ጉባዔ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ጉባዔ ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፤

13. Powers and Duties of chairperson of Regional Commission

The Chairperson of the Regional Commission shall have the following powers and duties:

1. To convene and direct the meeting of the commission,

2. ለዳኝነት፣ ለፊጅስትራርነትና ለተከላካይ ጠበቃነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ያሟሉ እጩዎችን ስም ዝርዝር ከእጭር የሕይወት ታሪካቸው መግለጫ ጋር አዘጋጅቶ ለጉባዔው ያቀርባል፤

3. በጉባዔው ተቀባይነት ያገኙ እጩ ዳኞችን ለምክቤቱ ለሹመት ያቀርባል፤

4. ከጉባኤው አባላት መካከል ፀሐፊውን ያስመርጣል፤

5. እንደአስፈላጊነቱ ጉባኤውን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል።

14. የዞን ጉባዔ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የዞን ጉባዔ ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፤

2. ከጉባዔው አባላት መካከል ፀሐፊውን ያስመርጣል፤

3. እንደአስፈላጊነቱ ጉባዔውን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤

4. የጉባዔውን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በየጊዜው ለክልሉ ጉባዔ ሰብሳቢና የብሔረሰብ ም/ቤት በተቋቋሙት ዞን ደግሞ ለዚሁ ም/ቤት ጭምር የሥራ ዘገባ ያቀርባል።

ክፍል አራት

በዳኝነት ለመሾም ስለሚያበቁ መመዘኛዎች

15. ለዳኝነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

2. To prepare and direct the meeting of the commission, the names and profiles of candidate judges, registrars and defense lawyers,

3. To present to the Council the judges to be appointed following approval of the commission,

4. To cause the election of a secretary from among Commission members,

5. Where deemed necessary to represent the Commission in all its contacts with third parties.

14. **Powers and Duties of Chairperson of Zonal Commission**

Pursuant to this proclamation, the chairperson of the Zonal Commission shall have the following powers and duties:

1. To convene and direct the meetings of the Commission,

2. To cause the election of the Secretary from among the Commission members,

3. Where deemed necessary, to represent the Commission in all its contacts with third parties,

4. To make report to the Chairperson of the Regional Commission and including to the Nationality Councils established in a Zone, about the Commission's performance.

PART FOUR

Criteria for the Appointment of Judges

15. **Criteria for Judgeship**

ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች አሟልቶ የተገኘ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍ/ቤቶች እደረጃጀት ውስጥ በዳኝነት ለመሾምና ለማገልገል ይችላል::

1. ለፌዴራሉና ለክልሉ ሕገ-መንግሥታት ታማኝ የሆነ/ች፣
2. በህግ ትምህርት የሠለጠነ/ች/ና በቂ የሥራ ልምድ ያለው/ት፣
3. በታታሪነቱ/ቷ/ በሥነምግባሩ/ሯ/ መልካም ስም ያተረፈ/ች/፣
4. በዳኝነት መ.ያ ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆነ/ች/፣
5. የሕግ አውጭው ወይም ህግ አስፈፃሚው አካላት አባል ያልሆነ/ች/ ወይም የማናቸውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ/ች/::

16. ስለ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶችና እጩ ዳኞች አሿሿም

1. በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 68/3/ ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶችና የየደረጃው ፍ/ቤቶች እጩ ዳኞች በክልሉ ጉባዔ አቅራቢነት በም/ቤቱ ይሾማሉ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች፣ የከፍተኛና ወረዳ ፍ/ቤቶች ዳኞች ሹመት ለም/ቤቱ ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት የክልሉ ጉባዔ የሚመለከታቸው ብሔረሰብ ም/ቤቶች በእጩ ተሿሚዎቹ ላይ ያላቸውን አስተያየት የመጠየቅና የማካተት ግዴታ አለበት::

17. ስለዳኞች ከሥራ መሠናበት

በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተመድቦ የሚሠራ ማንኛውም ዳኛ ከዳኝነት ሥራው ሊሰናበት የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል:-

Any Ethiopian who:-

1. Is loyal to the Federal and Regional Constitutions;
2. Has legal training and has acquired adequate legal skills through experience;
3. Has a good reputation for his /her diligence, sense of justice and good conduct;
4. Consents to assuming judgeship; and
5. Is not member of the Legislative or Executive bodies, or any political organization, may be appointed and serve as a judge in courts of the Amhara National Regional State.

16. **Appointment of High Court Presidents and Candidate Judges**

1. Without prejudice to the provisions of Article 68(3) of the Constitution, the presidents of High Courts and Candidate judges of courts at all levels shall be appointed by the Regional Commission.
2. Notwithstanding the provision of sub-article 1 of this Article, the Regional Commission shall request and include the opinion of concerned Nationality Councils prior to the approval of the appointment of the presidents of High Courts of Nationality Zones and the Judges of High Courts and Woreda Courts.

17. **Discharging Judges**

The tenure of any judge at any level of responsibility in the Region may be relieved only on the following grounds:

1. ምክር ቤቱ በሚያወጣው የዲስፒሊን ደንብ መሠረት ዳኛው ጉልህ ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝና ጉባዔው እንዲነሳ ሲወሰንበት፤
2. እድሜው 60 አመት ሲሞላ፤
3. ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ ሲታየበት ወይም በህመም ምክንያት የዳኝነት ሥራውን ማከናወን ሲያዳግተው፤
4. በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ፤
5. ዳኛው ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግና የ3 ወር ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ ሲሰጥ፤
6. ዳኛው ለሌላ መንግሥታዊ የሥራ ኃላፊነት ሲሾምና ሹመቱን ሲቀበል::

18. ስለ ሬጅስትራሮችና ተከላካይ ጠበቆች ከሥራ መሠናበት

ማንኛውም ሬጅስትራር ሆነ ተከላካይ ጠበቃ ከሥራ መሠናበት የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው:-

1. በህግ የተደነገገ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ፤
2. ሥራውን ለመልቀቅ የሰንብት ጥያቄ ሲያቀርብ፤
3. ጉልህ የሆነ ጥፋት ፈጽሞ በመገኘቱ ከሥራ ኃላፊነቱ እንዲነሳ በጉባዔው ሲወሰንበት፤
4. በችሎታ ማነስ ምክንያት የተመደበበትን የሥራ ኃላፊነት መወጣት ሲያዳግተው፤
5. በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ::

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. የይግባኝ አቤቱታ

1. Where he is found guilty of breach of disciplinary conduct set by the Council and where the Commission decides that he be removed;
2. Where he has attained the age of 60;
3. Where it is decided that he is of manifest incompetence and inefficiency;
4. Where is charged with a criminal offence and found guilty of same.
5. Upon resignation, subject to a 3-month prior notice;
6. Where he consents to an appointment to serve in a position of another governmental responsibility.

18. Discharge of Registrars and Defense Lawyers

Any registrar or defense lawyer shall be relieved of duty on the following grounds:

1. Where he has reached a retirement age;
2. Where he submits a letter of resignation;
3. Where the Commission decides on his discharge on grounds that he committed an offence;
4. Where it is decided that he is of manifest incompetence or inefficiency;
5. Where he is found guilty of a criminal offence.

PART FIVE
Miscellaneous Provisions

19. Lodging of Appeals

1. በዞን ጉባዔ ውሣኔ ያልተስማማ ማናቸውም ሰው ውሣኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፣

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጉባዔ ጉዳዩን መርምሮ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

20. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ጉባዔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን አስተዳደር ነክ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

21. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 12/1988 ዓ/ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

22. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
መጋቢት 23 ቀን 1994

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

1. Any person who does not agree with the decision of the Zonal Commission may lodge a complaint to the Regional Commission within 30 days of the decision.

2. Without prejudice to Article 6(5) of this Proclamation, the decision given by the Regional Commission following a consideration of the case shall be final.

20. Regulation Issuing Authority

The Regional Commission may issue any administrative regulation deemed essential for executing this Proclamation.

21. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Proclamation for Establishing the Judicial Administration Commission of Amhara National Regional State No. 12/1996 has been repealed and replaced by this Proclamation.

2. Any law, regulation or directive or a convention shall not be applicable to the case covered by this Proclamation.

22. Effective Dates

This Proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the Zikre Heg Gazette.

Done at Bahir Dar, this day of April 1,2002

Yosef Retta
President of The Amhara National Regional State